# ያልጠፋነው

ያልጠፋነው በእግዚአብሔር ምህረት የተነሳ ነው (፪)
ቸርነቱ ከቶ አያልቅምና )
ርህራሄው ከቶ አያልቅምና )
ይገባዋል ክብርና ምስጋና ) (፪)

ፈታኝ ሲያንገላታን በባህር ስንሄድ
ማዕበል ተነስቶ ያ የሥጋ ሞገድ
ህይወት ስትመዘን ልባችን ሲናወጥ
ለጠላት ሳይሰጠን አደረገን ዘመድ

አዝ...

ስለሆነ እሮሮ ፈጥኖ የማይቀየር
በንስሃ ኖረን ባንሄድ ወደ አለም
ምስክር ነን እኛ አይተናል ማዳኑን
በሱ ተማርከናል ቀምሰን ቸርነቱን

አዝ...

በበደልነው በደል ማረን እንላለን
ካንተ ተለይተን ወዴት እንሄዳለን
አለም የማያውቀው የማይመረምረው
በውስጣችን አለ እኛ የምናመልከው

አዝ...

እንግዲህ አልፈልግም የሸንጋይ ምላስ
ቃልህ ይቆጣጠረኝ በሥጋም በነፍስ
አንተ ካከበርከኝ ማን ያዋርደኛል
አይኔን ከሰው አንሳው አሁንስ በቅቶኛል

አዝ...

www.HolyTrinityEOTCNY.org